# የአእምሮ ጤንነት፣ የንቃተ ህሊና ወይም የእድገት እክሎች ያሉባቸው ግለሰቦች የሚቀርብ ፍትሀዊ የመኖሪያ ቤት፡

## ለመኖሪያ ቤት አቅራቢዎች የተዘጋጀ መመሪያ




www.hud.gov/fairhousingን ይጎብኙ፣ ወይም ለብሔራዊ የመድልዎ ማስመር በስልክ ቁጥር 1-800-669-9777 ወይም 1-800-877-8339 (የፌደራል ሪሌይ) ይደውሉ

Amharic

## የቤት አቅራቢዎች ማወቅ ያለባቸው ነገር?

ፍትሃዊ የመኖሪያ ቤት ህጎች የአእምሮ ጤንነት፣ የንቃተ ህሊና ወይም የእድገት እክሎች ያሉባቸው ግለሰቦችን ጨምሮ በአካል ጉዳተኞች ላይ ሚደረግን የመኖሪያ ቤት  መድልዎን ይከለክላል። የአእምሮ ጤንነት፣ የንቃተ ህሊና እና የእድገት እክሎች ያሉባቸው ግለሰቦች በተቋማት እና በሌሎች በተለዩ ቦታዎች እንዲኖሩ መገደድን ጨምሮ ብዙ አይነት መድልዎ ያጋጥማቸዋል፡፡ ለአካል ጉዳተኞች ከመድሎ ነፃ ሆነው ለመኖር የሚያስችሏቸው ተመጣጣኝ፣ የተቀናጁ፣ ማህበረሰብ ተኮር የሆኑ አማራጮች መኖር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡  አካል ጉዳተኛ ግለሰቦች የሚያስፈልጓቸው አንደ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች፣ ተንከባካቢ ወይም ረዳት፣ ወይም ሌሎች የአጭር ወይም የረጅም ጊዜ አገልግሎቶች ወይም ድጋፎች  የመሳሰሉ ማናቸውንም ድጋፎች ከማግኘት ጋር በማኅበረሰቡ ውስጥ ራሳቸውን ችለው የመኖር መብት አላቸው። አካል ጉዳተኛ ግለሰቦች በተቋማት ውስጥ እንዲቆዩ እንዳይገደዱ ለማድረግ ማህበረሰብን መሠረት ያደረጉ የቤት አማራጮችን ማግኘትም አስፈላጊ ነው።

አካል ጉዳተኛ ግለሰቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እና ነፃ የመሆን መብቶች አሏቸው። አንዳንድ አካል ጉዳተኞች በተወሰኑ እንቅስቃሴዎች ላይ እርዳታ ሊፍልጉ ወይም  ግድ ሊሆንባቸው ይችላል  እንዲሁም የጠበቃ፣ ተወካይ ወይም የአሳዳጊ አገልግሎቶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ወቅት የመኖሪያ ቤት አቅራቢዎች ጠበቆች እና ተወካዮች በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ በተገቢው ሁኔታ መሳተፋቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። የመኖሪያ ቤት አቅራቢዎች ለግለሰቡ በሚጠቅመው ነገር ላይ የአባትነት ወይም የአድሎአዊ ውሳኔ መወሰን የለባቸውም።

## የአካል ጉዳትን መድልዎ የሚከለክሉ ፍትሃዊ የመኖሪያ ቤት ሕጎች

የፍትሃዊው የመኖሪያ ቤት ሕግ፣ የተሃድሶ ህጉ አንቀፅ 504 እና የአሜሪካውያን የአካል ጉዳተኞች ህግ፣ በአካል ጉዳተኞች ላይ ሚደረግን የመኖሪያ ቤት አድልዎ ይከለክላሉ። እነዚህ ህጎች ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ፣ አካል ጉዳተኛ ላልሆኑ ግለሰቦች የሚሰጠውን የመኖሪያ ቤት እድል በተመሳሳይ አካል ጉዳተኞችም እንዲያገኙ ያስገድዳሉ። ለእነዚህ ጥበቃዎች መብት ያላቸው ግለሰቦች አንድ ወይም ከዚያ በላይ ዋና ዋና የአኗኗር እንቅስቃሴዎችን በእጅጉ የሚገድቡ የአካል ወይም የአእምሮ እክሎች ያለባቸውን ያጠቃልላሉ።

## ጥበቃ ሚደረግላቸው የአእምሮ ጤንነት፣ የንቃተ ህሊና እና የእድገት እክሎች ምሳሌዎች ምንድናቸው?

ጥበቃ ሚደረግላቸው አካል ጉዳቶች እንደ ኦርጋኒክ የአንጎል ሲንድሮም፣ ድብርት፣ ጭንቀት፣ ባይፖላር ዲስኦርደር፣ ድህረ-አሰቃቂ ክስተት የጭንቀት በሽታ (PTSD)፣ የተወሰኑ የመማር እክሎች፣ ኦቲዝም፣ ዝቅተኛ የአእምሮ ጤንነትን፣ የአሰቃቂ ክስተት አእምሯዊ ጉዳቶች፣ የአልኮል ሱሰኝነት እና የአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኝነት (በአሁኑ ወቅት ሕገ-ወጥ ዕፅ አጠቃቀም ምክንያት ከሚመጣ ሱስ በስተቀር) የሆኑ የአእምሮ ጤንነት፣ የሳይኮሎጂ፣ የአስተሳሰብ እናም የእድገት ሁኔታዎች ያለባቸውን ጨምሮ በእነዚህ ላይ ብቻ ሳይወሰን ያጠቃልላሉ። **የአእምሮ ጤንነት፣ የንቃተ ህሊና ወይም የእድገት እክሎች ያሉባቸው ግለሰቦች በተለምዶ የመኖሪያ ቤት መድልዎ የሚያጋጥማቸው እንዴት ነው?**

በፍትሃዊ የመኖሪያ ቤት ሕጎች መሠረት አካል ጉዳተኝነትን መሰረት በማድረግ በግለሰቦች ላይ መድሎ ማድረግ ሕገወጥ ነው። በፍትሃዊ የመኖሪያ ቤት ህጎች የተከለከሉ የመድልዎ ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው፡

- የመኖሪያ ቤት አቅራቢው ሁሉንም አመልካቾች ለአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች ብቻ ለሚቀርቡ መኖሪያ ቤቶች ብቁ መሆናቸውን ለመወሰን የአካል ጉዳት ያለባቸው ስለ መሆኑ ካልጠየቀ በስተቀር በማመልከቻ ሂደቱ ወቅትግለሰቡ አካል ጉዳተኛ ስለመሆኑ ወይም ስለ አንድ አካል ጉዳተኝነቱ ተፈጥሮዋዊ ባህሪ ሲጠየቅ፣
- በአካል ጉዳተኝነቱ ምክንያት ለአንድ ግለግለሰብ ወይም ከግለሰቡ ጋር አብሮ ለሚኖር ሰው ስለ መኖሪያ ቤት መረጃ ለመስጠት ወይም ለማሳየት ፈቃደኛ አለመሆን
- በአካል ጉዳተኝነቱ ምክንያት ለአንድ ግለግለሰብ መኖሪያ ቤት ለማከራየት ወይም ለመሸጥ ፈቃደኛ አለመሆን
- አመልካች በድርጅታዊ አሠራር ወይም በቡድን ቤት ውስጥ ስለኖረ ቤትን መከልከል
- በመኖሪያ ቤት ኪራይ ወቅት በአካል ጉዳተኝነት ምክንያት ከፍ ያለ ኪራይ ወይም የዋስትና ተቀማጭ ገንዘብን የመሳሰሉ የተለያዩ ውሎችን ወይም ሁኔታዎችን ማስቀመጥ

- አመልካች በድርጅታዊ አሠራር ውስጥ በመኖሩ መከኒያት የተለያዩ ሰነዶችን ወይም ሁኔታዎችን በመኖሪያ ቤቱ ላይ ማስቀመጥ፣ ለምሳሌ እንደ ተጨማሪ ሰነዶችን መጠየቅ ወይም ተጨማሪ የማረጋገጫ ማጣሪያ ሂደትን ማድረግ

- ተመጣጣኝ ማረፊያን ለመስጠት ፈቃደኛ ያለመሆን ወይም ለግለሰቡ ወይም ከግለሰቡ ጋር አብሮ ለሚኖር አካል ጉዳተኛ የሆነ ሰው ቤታቸውን በእኩል እድል ለመጠቀም ወይም በመኖሪያ ቤታቸው ለመደሰት አስፈላጊ ሊሆንባቸው የሚችሉ ምክንያታዊ ማሻሻያዎችን ያለመፍቀድ

- በአካል ጉዳተኝነት ምክንያት አንድ ሰው በተወሰኑ ክፍሎች ወይም በመኖሪያ ቤት ግቢ ውስጥ እንዳይኖር መገደብ

- በአካል ጉዳት ምክንያት ጠንካራ የማጣሪያ መስፈርቶችን መጠቀም

- አካል ጉዳተኛ ግለሰቦች ለመኖሪያ ቤት እንዳያመለክቱ በአድሎአዊ መንገድ ማስታወቂያ መስራት

- በአካል ጉዳተኝነት ምክንያት ነዋሪን ወይም ከነዋሪው ጋር አብሮ ለሚኖር አካል ጉዳተኛ የሆነ ሰውን ማስወጣት

- በአካል ጉዳተኝነት ምክንያት አንድን ሰው ወይም ከግለሰቡ ጋር አብሮ ለሚኖር አካል ጉዳተኛ የሆነ ሰው ላይ ትንኮሳ ማድረግ

- ስለ ህክምና ወይም መድሃኒቶች ጥያቄዎችን መጠየቅ

- አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ አካል ጉዳተኛ ግለሰቦች ብቻ በስብስብ በተያዙ የቤቶች ልማት ውስጥ ምደባን እንዲቀበሉ መጠየቅ

## በፍትሃዊ የመኖሪያ ቤት ህጎች መሠረት የሚፈቀዱ ተግባራት ምንድናቸው?

የመኖሪያ ቤት አቅራቢው አመልካቾች ላይ ላሉት መኖሪያ ቤቶች ማጣሪያ ሊያካሂድ እና ደንቦቹን እና ኮዶቹ ለሁሉም ሰዎች በተመሳሳይ መንገድ የሚተገበሩ፣ አድሎአዊ ካልሆኑ እና የመኖሪያ በቱ አቅራቢዎች ለአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች አስፈላጊ በሚሆኑበት ግዜ የፖሊሲዎች፣ ልምዶች፣ ህጎች እና ኮዶች ተመጣጣኝ ማሻሻያዎችን ካደረጉ የቤት አቅራቢው አመልካቾችን ለሚገኘው መኖሪያ ቤት ማጣሪያ ሊያካሂድ እንዲሁም ህጎች እና ኮዶችን ሊያወጣ ይችላል። የመኖሪያ ቤት አቅራቢዎች አካል ጉዳተኞችን በፍርሃት፣ በአድልዎ ወይም በአጠቃላይ በመለየት በደል ማድረስ አይችሉም።

## ምክንያታዊ ማረፊያዎች እና ማሻሻያዎች ምንድናቸው?

ተመጣጣኝ ምክንያታዊ ጥቅሞች እና ማሻሻያዎች ለአካል ጉዳተኞች መኖሪያ ቤትን የመጠቀም እና የመደሰት እኩል እድል ለመስጠት በሕጎች፣ ፖሊሲዎች፣ አሰራሮች፣ አገልግሎቶች ወይም የመኖሪያ ቤት ላይ ሚደረጉ ማሻሻያዎች እና ለውጦች ናቸው። በHUD በሚታገዙ ቤቶች ውስጥ፣ የመኖሪያ ክፍሎች፣ የህዝብ እና የጋራ መጠቀሚያ ቦታዎች ላይ የሚደረጉ መዋቅራዊ ለውጦች የመኖሪያ ቤት አቅራቢው ሊያቀርባቸው ከሚገቡ ምክንያታዊ ማሻሻያዎች ስር ይመደባሉ። አንዳንድ ምክንያታዊ የማሻሻያ ወይም የተሻለ ለውጥ ጥያቄዎች ምሳሌዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡

- "የቤት እንስሳት ያለመፍቀድ" ፖሊሲ በሚኖርበት ጊዜ ረዳት እንስሳ እንዲኖር መጠየቅ

- ማመልከቻ ወይም ሌላ የወረቀት ሥራን ለመሙላት እርዳታ መጠየቅ

- የመኖሪያ ቤት አቅራቢው ረዳት ወይም ሌሎች የድጋፍ አገልግሎቶችን እንዲፈቅድ መጠየቅ

- ውስን የማመልከቻ ጊዜዎችን ማራዘም እና አመቺ የማመልከቻ ሂደቶችን ወይም ቦታዎችን መፍቀድ

- የማኅበራዊ ዋስትና የአካል ጉዳት ቼክ ወይም የአጭር ወይም የረጅም ጊዜ የአካል ጉዳት ክፍያ እስኪቀበሉ ኪራይ የሚከፈልበትን ቀን እንዲለወጥ መጠየቅ

- ከእንቅስቃሴ ወይም ከሴንሰር ፍላጎቶች ጋር በተዛመደ መኖሪያ ወይም የጋራ አካባቢ ላይ ተጨባጭ ለውጦችን መጠየቅ

- ከአካል ጉዳተኝነት ጋር በተዛመደ ምክንያት በጊዜ ለጥያቄዎች መልስ ካልሰጡ በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ እንዲቆዩ መጠየቅ

- አመልካች በተጠባባቂዎች ዝርዝር አናት ላይ ሲደርስ ነገር ግን እንደ ህክምና ወይም ሆስፒታል በመሳሰሉ ከአካል ጉዳተኝነት ጋር በተዛመደ ምክንያት መንቀሳቀስ ባለመቻሉ ምክንያት ወደ አንድ ክፍል ለመግባት ተጨማሪ ጊዜን መጠየቅ

- ተከራይ በሆስፒታል ምክንያት ውስን ወይም ጨራሹንም የኪራይ ወይም የሥራ ስምሪት ታሪክ በማይኖረው ጊዜ እንደ ማህበራዊ ሰራተኛ ያሉ አማራጭ ዋቢዎችን መቀበል

# የአእምሮ ጤንነት፣ የንቃተ ህሊና ወይም የእድገት እክሎችላሉባቸው ግለሰቦች የሚቀርብ ፍትህዊ የመኖሪያ ቤት፡ ለመኖሪያ ቤት ማላማላ አቅራቢዎች የተዘጋጀ መመሪያ






## አካል ጉዳተኛ ግለሰብ ምክንያታዊ  መኖሪያ ወይም ማሻሻያ ከጠየቀ የመኖሪያ ቤት አቅራቢ ምን ዓይነት መረጃ ሊጠይቅ ይችላል?

የአካል ጉዳቱ እና የጥያቄው ፍላጎት ለቤት አቅራቢው ግልጽ ወይም አስቀድሞ የታወቀ ከሆነ አቅራቢው ሌላ ማንኛውንም መረጃ መጠየቅ አይችልም። የቤት አቅራቢዎች በአካል ጉዳተኝነት ምክንያት የተጠየቀ ተመጣጣኝ መኖሪያ ወይም ማሻሻያ አስፈላጊ ሊሆን እንደሚችል ለመገምገም አስፈላጊ የሆነውን መረጃ መጠየቅ ሚችለው የጠያቂው አካል ጉዳት ግልጽ ወይም የማይታወቅ ካልሆነ ብቻ ነው። የቤት አቅራቢዎች ጠያቂው ተመራጭ የሆኑ ቅጾች ወይም ቅደም ተከተሎችን ባይጠቀምም ምክንያታዊ የመኖርያ እና የማሻሻያ ጥያቄዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው። የመኖሪያ ቤት አቅራቢዎች በዚህ ሂደት ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ከግለሰቡ ጋር  በተገናኘ ሂደት ውስጥ ሊሳተፉ ይችላሉ፣ ነገር ግን ይህን ጥያቄውን ከመከልከላቸው በፊት ማድረግ አለባቸው።

### ፍትሃዊ መኖሪያ ቤት ጥሩ ንግድ ነው። ብሎም ሕግም ነው።

የበለጠ መረጃ ለማግኘት www.hud.gov/fairhousing ይጎብኙ ወይም የአካባቢዎን የHUD ቢሮ፣ የግዛት ወይም የአካባቢ ፍትሃዊ የቤቶች ድርጅትን ያነጋግሩ፡፡ እባክዎ የበለጠ ለማወቅ የሚከተሉትን ሊንኮች ይጎብኙ፡

- በፍትሃዊ የመኖሪያ ቤት ህጎች የተደነገጉ የአካል ጉዳተኞች መብቶች
- ክፍል 504 በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች
- በፍትሃዊ የመኖሪያ ቤት ሕግ ስር የተደነገጉ ምክንያታዊ ፍላጎቶች
- በፍትሃዊ የመኖሪያ ቤት ሕግ ስር የተደነገጉ ምክንያታዊ ለውጦች
- በፍትሃዊ የመኖሪያ ቤት ሕግ ስር የግለሰብን እንስሳን እንደ መክንያታዊ ፍላጎት የማምጣት ጥያቄ መገምገም
- የHUD የኦምስቴድ ግቦችን የማሳካት ሚና መግለጫ